# ጾምና ጸሎት

**"ጴጥሮስም በወኅኒ ይጠበቅ ነበር፤ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር። ሄሮድስም ሊያወጣው ባሰበ ጊዜ፥ በዚያች ሌሊት ጴጥሮስ በሁለት ሰንሰለት ታስሮ ከሁለት ወታደሮች መካከል ተኝቶ ነበር፤ ጠባቂዎችም በደጅ ፊት ሆነው ወኅኒውን ይጠብቁ ነበር። እነሆም፥ የጌታ መልአክ ቀረበ በቤትም ውስጥ ብርሃን በራ፤ ጴጥሮስንም ጎድኑን መትቶ አነቃውና። ፈጥነህ ተነሣ አለው። ሰንሰለቶቹም ከእጁ ወደቁ" (ሐዋ 12፡5-7)።**



**ቀኖቹ** - November 30 - December 4, 2015

**ሰዓትና ቦታ** - የሕብረት ጸሎት

- ሰኞ ፡ አሊመኒ ቡሎቫርድ - 7፡00pm
- ማክሰኞ ፡ ቡካነ - 7፡00pm
- ሮብ፡ አሊመኒ - 7፡00pm
- ሐሙስ ፡ ቴሌግራፍ - አክላንድ - 6:30pm
- አርብ ፡ አሊመኒ : 7፡00pm

**ማሳሰቢያ፡** በዚህች የጾምና ጸሎት አነስተኛ መመሪያ (booklet) ውስጥ ስለጾምና ጸሎት ከዚህ በታች የተጻፈው አስተምህሮ በዳላስ በምትገኘው የኢትዮጵያውያን ባፕቲስት ቤ/ክ የተዘጋጀ ነው። ይህንንም እንድንጠቀምበት የቤ/ክርስቲያኒቷ መሪዎች ስለፈቀደሉን ከልብ እናመሰግናለ።

## ፆም ና ጸሎት በአማኝ ህይወት!!

በጸጋ መዳናቸውን አስደግፈው መጾምን በተመለከተ "አያስፈልገንም" የሚሉ አሉ ። ሌሎች ደግሞ ወደ ጌታ መቅረቢያ ሥራቸው አድርገው "ያስፈልጋል" ይላሉ። የሁለቱም ወገኖች ዕይታ ጽንፈኛነት አለው። በመሰረቱ ብዙ የእግዚአብሔር ወዳጆችና አገልጋዩች ጾመዋል። የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ (40 ቀናት)፥ ንጉሡ ዳዊት (7 ቀናት)፥ ንግሥት አስቴር (3 ቀናት)፥ ሐዋሪያው ጳውሎስ (3 ቀናት)፥ እሥራኤል (1 ቀን) መጾማቸውን ለአብነት ያህል ከቃሉ ማየት ይቻላል።
መጾምን እንደሃይማኖተኝነት ሥራ አድረገን የምንመካበት ከሆነ በጌታ ዘንድ ተቀባይነት ከማጣቱም በላይ ዕዳ የሚያመጣ ይሆናል። ትህትና የለበትምና።

- **ለታይታ አይሁን!!!** "ስትጦሙም፥ እንደ ግብዞች አትጠውልጉ፤ ለሰዎች እንደ ጦመኛ ሊታዩ ፊታቸውን ያጠፋሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን ስትጦም፥ በስውር ላለው አባትህ እንጂ እንደ ጦመኛ ለሰዎች እንዳትታይ ራስህን ተቀባ ፊትህንም ታጠብ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል።" ማቴ. 6፡ 16-18
- **ጾም ና ጸሎት እግዚአብሔርን ማዕከል ያደረገ መሆን አለበት።** እርሱን ለመፈለግ፥ እርሱን ለማምለክ ና ለእርሱ ፈቃድ ለመገዛት። ነቢይቷ ሐና "በጾምና በጸሎትም ሌሊትና ቀን እያገለገለች ከመቅደስ አትለይም ነበር" (ሉቃ. 2፡ 37)። በአንጾኪያም የነበሩት ያደርጉት ይህንኑ ነበር። "ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ፣ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ" ( ሐዋ. 13፡ 2)በነቢዩ ዘካሪያስ የመጣው መልዕክት ይህ ነበር። እንዲህ ሲል

"ለምድሩ ሕዝብ ሁሉ ለካህናትም እንዲህ ብለህ ተናገራቸው። በዚህ በሰባው ዓመት በአምስተኛውና በሰባተኛው ወር በጾማችሁና ባለቀሳችሁ ጊዜ፥ በውኑ ለእኔ ጾም ጾማችሁልኝ?" (ዘካ.7፡ 5) ለጌታ ና ወደ ጌታ ካልጾምን ከንቱ ይሆንብናል።

- **በጾምን ቀን ፈቃዱን ለማድረግ እንትጋ** "ስለ ምን ጾምን፥ አንተም አልተመለከትኸንም? ሰውነታችንንስ ስለ ምን አዋረድን፥ አንተም አላወቅህም? ይላሉ። እነሆ፥ በጾማችሁ ቀን ፈቃዳችሁን ታደርጋላችሁ፥ . . . በውኑ ይህን ጾም፥ በእግዚአብሔርም ዘንድ የተወደደ ቀን ትለዋለህን? . . ." ትን. ኢሳ. 58፡ 1-14 እንግዲያስ በጾምን ቀን እርሱን ደስ የሚያሰኘውን ሌሎችን የሚጠቅመውን ሁሉ እናድርግ። ያን ጊዜ እግዚአብሔርም ይሰማናል እርሱም፡- እነሆኝ ይለናል።
- **ስለ ልዩ ልዩ ጉዳዮች ጾም ና ጸሎት ይደረጋል፤ ጌታም እጁን ልኮ ይረዳል።** በጦርነት ጊዜ ለድል (2 ዜና 20), በበደል ለንስሃ (ዮናስ 1-4), በጉዞ ላይ ለጥበቃ (እዝራ 8), አጋንንትን በኃይል እንዲወጡ ለማድረግ (ማቴ. 17), ትልልቅ ችግሮች በቤተሰብ፤ በቤተክርስቲያንም ሆነ በሀገር ደረጃ ለመፍታት ጾምና ጸሎት ይደረጋል። ጌታም ታምራትን ያደርጋል።

**ግንዛቤ፡-** መጾም የተለያየ መንገድ አለው። ከምግብ ና ከውኃ በመለየት (ዘዳ.9፡9)፥ ቅባት ካለበት ማለፊያ ምግብ በመቆጠብ (ዳን. 10፡3)። ሰውነታችን በፍጥረቱ ያለ ውኃ ለመቆየት ስለሚከብደው ረዥም ቀናት ጾም ከምግብ ተለይቶ ውኃ እየወሰዱ ይደረጋል። ለረዥም ቀናት በተከታታይ የሚወሰዱ የጾም ቀናትን መጨረስ በሚፈለግበት ጊዜ ለጤንነት እንቅፋት እንዳይሆን ከሚጠጡ ፈሳሾች ጀምሮ ወደ ሚታኘኩ ምግቦች የመሸጋገር ብልሃት አስፈላጊ ነው።

ትን. ዘካ. 8፡ 19 "የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- የአራተኛው ወር ጾም የአምስተኛውም የሰባተኛውም የአሥረኛውም ወር ጾም ለይሁዳ ቤት ደስታና ተድላ የሐሤትም በዓላት ይሆናል . . ."

**ቀን** - ሰኞ November 30, 2015

**የዕለቱ ንባብ**፡- 1 ዜና 7 በሙሉ ይነበብ።

**መሪ ጥቅስ ፡ 1 ዜና 7፡ 14** *"በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፥ ፊቴንም ቢፈልጉ፥ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፥ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፥ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፥ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ"* **ምሳሌ 28፡13** *"ኃጢያአቱን የሚሰውር አይለማም የሚናዘዛትና የሚተዋት ግን ምህረትን ያገኛል"።*

### የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡

1. ራስን መመርመር ለተሃድሶ ጠቃሚ ነው። ንስሃ በመግባት ምህረት ለመቀበል የመጀመሪያው እርምጃ መበደላችንን መገንዘብና መናዘዝ ነው። ከኃጢያታችን ሊያጥበን፤ በደላችንንም ሊያነጻልን የሚችል የክርስቶስ ደም ብቻ ነው። ስለዚህ በእምነት "ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ፥ ከኃጢአቴም አንጻኝ" እንለዋለን።
2. ንስሀ ማለት መናዘዝ ብቻ እንዳልሆነና ነገር ግን የአመለካከት ወይም የመንገድ ለውጥ ማድረግ ነውና ወደ ተውነውና ወደጣልነው ነገር እንዳንመለስ ጌታ በቃሉና በመንፈሱ እይታችንን እንዲያቀናልን እና ክፉ ምኞትን ከእኛ እንዲያወጣ እንጸልያለን (ያቆ 1፡14)።

### የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች

1. በምድራችን በኢትዮጵያና፥ በኤርትራ ውስጥ ስለአለው ክፉ አምልኮ፣ ጥንቆላና ማንኛውም የጨለማ ሥራ እንዲሁም እስከዛሬ ስለፈሰሰው ደም እያሰብን በንስሃ መቆየት። በተጨማሪም ለመንግስት መሪዎች፣ አስተዳዳሪዎች ሁሉ ማስተዋልና ጥበብ እንዲሰጥ እንጸልያለን።
2. የጀመረነውን የጾምና ጸሎት ፕሮግራም በጥሩ ሁኔታ እንድንፈጽም ወደ ጌታ ልመና ማቅረብ። እንቅፋት ከሰው ሁሉ ተወግዶ ሳንተጓጎል ሁላችንም በአንድ ልብ በድል እንድንፈጽም እንጸልያለን።
3. በጾምና በጸሎት በፊቱ የሚቆዩትን የጌታ መንፈስ በሙላት እንዲጎበኝ ይህም በጌታ ፊት የመሆን ልምምድ የግል መንፈሳዊ ድል ምክንያት እንዲሆንላቸው እንጸልያለን።

4. በ2015 ዓ/ም ወደ ማለቂያው ስለሆነ በዚህ ዓመት ጌታ ቤ/ክንንና ቅዱስንን ስለረዳ፥ በምህረቱና በጸጋው ደግፎ ስላቆመን ጌታን ማመስገን(ኢሳ 43፤20-21)
5. በምንኖርባት በዚህች ሃገር (አሜሪካን) ስላለው የከፋና የጨለማ ስራ ንስሃ እንገባለን። ለመንግስት ባለሥልጣኖችና በማስተዳደር ላይ ላይ ላሉ መሪዎች ሁሉ (በቢዝነስ፣ በትምህርት፣ በሕክምና በፖለቲካና ማንኛውም የአስተዳደር ተቋሞች ላሉ መሪዎች ሁሉ እግዚአብሔርን መፍራት፣ ጥበብና ማስተዋል እንዲሰጥ እንጸልያለን።
6. በዓለማችን ዙሪያ የንጹሃንን ደም በማፍሰስ የሚካሄድውን የሽብር (Terrorism) ጥፋት በመቃወም ይህ የጨለማና የግድያ መንፈስ ጨርሶ እንዲጠፋ እንጸልያለን። ከዚህና ከተለያዩ ጦርነቶች የተነሳ በዓለም ዙሪያ ስለተሰደዱ ሰዎች አዛውንትና ህጻናት እንጸልያለን።

**የግል ወይም ስለ ሌሎች የምንጠይቃቸው የጸሎት ርዕሶች**

1. ______________________________
2. ______________________________
3. ______________________________
4. ______________________________
5. ______________________________

**ማስታወሻ፡**

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

______________________________

**ቀን** – ማክሰኞ December 1, 2015

**የዕለቱ ንባብ፡** - ሐዋ ሥራ 1፡ 1- 25

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡** -

1. ጌታ ስለሚበልጠውና ስለከበረው የእግዚአብሔር መንግስት መምጣት ቢነግራቸውም ልባቸው በምድራዊው የእስራኤል መንግስት መመስረት ላይ ተጣብቆ ነበር። የእኛም ልብ ከተያዘበት ከራሳችን ነገር ወደሚበልጠውና የጌታ ልብ ወዳለበት ወደ ከበረው ወደ እርሱ ነገር ጌታ እንዲመልሰው እንጸልያለን (ት.ሐጌ 1፤5 እና ቁ 7)

2. ከ12 ሐዋርያት አንዱ ይሁዳ ከሰማይ የመጣለትን ጥሪ እንዳቃለለና በራሱ ፈቃድ እንደተዋት ከሰማይ የተጠራንበት ጥሪ የከበረ እንደሆነ አስተውለን በተጠራንበት ጥሪ ልክ መኖር እንጂ ማፈግፈግ እንዳይሆንብን ጸጋ እንጠይቃለን። (ሐዋ 1፡25)

3. ሐዋ 1፡8 እንደሚያዘን ለጌታ ሞትና ትንሳዔ ከቤት ጀምረን እስከ ዓለም ሁሉ ምስክሮች እንድንሆን እንጸልያለን።

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡** -

1. በዓለም ዙሪያ ስለጌታ ስለሚሰደዱ ቅዱሳን እንማልዳለን። ጌታ በርኅራኄው እንዲታደጋቸው ምስክርነታቸውንና አገልግሎታቸውን ውጤታማ እንዲያደርግ እንጸልያለን።

2. ባለፉት አራት ዓመቶች በቤ/ክርስቲያናችን ጌታን ተቀብለው ስለተጠመቁት ወገኖቻችን መንፈሳዊ ሕይወት እድገት እንጸልያለን። ቤ/ክ እነዚህን ወገኖች በቃሉ እውቀትና በአገልግሎት ለማሳደግ ትኩረት እንድትሰጥ፤ እንዲሁም ይህን ለማድረግ የሚያስችላት አቅምና ችሎታ እንዲኖራት እንጸልያለን።

3. የቤተክርስቲያን አባላቶቻችን ለቤተሰቦቻቸው፣ ለዘመዶቻቸው፣ ለጉደኞቻቸው፣ ለሥራ ባልደቦቻቸውና ለጎረቤቶቻቸው ወንጌልን የመመስከር ትኩረት፣ ትጋት እንዲያገኙ እንጸልያለን።

4. በቤተክርስቲያናችን ውስጥ ለአዋቂዎች መንፈሳዊ ዕድገት የሚጠቅም የሰንበት ትምህርት እንዲጀምር እንጸልያለን።

5. የቤተክርስቲያንችን የሚዲያ ሚኒስትሪ ተጠናክሮ ከቤተክርስቲያናችን ውጭ ላሉ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት የሚጠሙ ወገኖችን ማገልገል የሚችልበት አቅምና ችሎት እንዲያገኝ እንጸልያለን። በዓለም ዙሪያ የተበተኑት ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን ወገኖቻችንን በዚህ ረገድ ቤተክርስቲያን ማገልግል እንድትችል ለዚህ ስራ የጌታ መንፈስ ሰዎችን እንዲያነሳሳ እንጸልያለን።

6. ቤተክርስቲያናችን በሳንፍራንሲስኮና በኦክላንድ ከተሞች ውስጥ ብርሃንዋ ደምቆ ብዙዎችን ወደ ጌታ የምትጠራ እንድትሆን እንጸልያለን።

7. በቤይ ኤሪያ ያሉ አብያተክርስቲያናት የአለም ብርሀንነታቸው ደምቆ እንዲታይና በቃልም ሆነ በስራ የበረቱ እንዲሆኑ እንጸልያለን።

## የግል ወይም ስለ ሌሎች የምንጠይቃቸው የጸሎት ርዕሶች

1. ______________________________
2. ______________________________
3. ______________________________
4. ______________________________
5. ______________________________

**ማስታወሻ፡**

**ቀን** - ረቡዕ December 2, 2015

**የዕለቱ ንባብ፡** - ሐዋ ሥራ 2፡1-47

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡** -

1. ሐዋ ሥራ 2፡1-4 ከእግዚአብሔር ዘንድ የተስፋ ቃላቸውን ሲጠብቁ ሳለ በአንድ ልብ ሆነው ፊቱን በጸሎት ና በአምልኮ ይፈልጉ እንደነበረ ጌታ በአንድነት በመያያዝ የመንፈስን አንድነት በመጠበቅ ተልእኮአችንን መወጣት እንድንችል ትጋትን እንዲሰጠን እንጸልያለን።(ኤፌ 4፤3)

2. ቤተ ክርስቲያን በመንፈስ ቅዱስ መውረድ እንደተወለደችና እንዳደገች ለሙሽራውም የምትዘጋጀው በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው። ቢሆንም መንፈስ ቅዱስ ስብእና እንዳለው አካል ለእርሱ ንቁ አይደለንም ፤አምላክነቱን እውቅና እየሰጠን ላልታዘዝነውና ላስመረርነው ነገር እንደግለሰብና እንደህብረት ንስሀ እየገባን ከእርሱ ጋር ህብረታችንን እናድሳለን ።

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡** -

1. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የቤት ለቤት ህብረቶችን በተመለከተ
    - በተሻለ መልኩ የተጠናከሩ እንዲሆኑ ጌታ እንዲረዳን
    - ለምናጠናው ለጌታ ቃል መልእክት ታማኞች እንድንሆን እንዲያግዘን
    - ጥናቱን የሚያዘጋጁ፣ የሚያስተባብሩ፣ የሚመሩ አገልጋዮች እና የሚሳተፉም ሁሉ ህይወታቸውና ኑሮአቸው እንዲባረክ
    - የአገልግሎቱን መሪዎችና የህብረት መሪዎችን ጌታ እየረዳ በእውቀትና በእረኝነት መንፈስ እንዲቀባቸው
    - በጥናቱና በህብረቱ የማይሳተፉ መሳተፍ እንዲችሉ ጌታ ነገሮችን እንዲያመቻችላቸውና ልባቸውን እንዲያነሳሳ

2. ስለ ሳምንታዊ የቤተክርስቲያን የህብረት አምልኮ ፕሮግራሞች እንጸልያለን።
    - የእሁድ ጠዋት ሳምንታዊ የአምልኮ ፕሮግራም ውጤታማ እንዲሆን ጌታ እንዲረዳን። ቅዱሳን ዋጋ በመክፈል፣ ቸል ሳይሉ መካፈል እንዲችሉ ጌታ እንዲረዳን።
    - የማክሰኞና የሐሙስ መደበኛ የአምልኮ ፕሮግራሞች ውጤታማ እንድሆኑ። በሳን ፍራንሲስኮና በኦክላንድ አካባቢ ያሉ ቅዱሳን በእነዚህ ፕሮግራሞች ተግተው እንዲካፈሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ልባቸውን በማነስሳት እንዲረዳን እንጸልያለን።
    - በሮብ ማታ የተጀመርው የእንግሊዘኛ ቋንቋ አምልኮ ፕሮግራም እንዲያድግና ወደ ቤተክርስትያንነት እንዲመጣ። በአለመኒ ቡሎቫርድ አካባቢ የሚኖሩትን ሰዎች በወንጌል መልዕክት መድረስ የምንችልበትን የመንፈስ ቅዱስ አቅምና ጸጋ እንዲሰጠን እንጸልያለን።
    - አርብ ማታ የተጀመርውን “አባይድ” ወይም “መኖር/መጠበቅ” የተባለውን የወጣቶች ፕሮግራም ጌታ እንዲባርክ። ይህ ፕሮግራም ለወጣቶቻችን መንፈሳዊ ህይወት ማደግና መጠበቅና በቤተክርስቲያናችን ዙሪያ የሚኖሩ ወጣቶችን በወንጌል በመድረስ በመሆን ውጤታማ እንዲሆን እንጸልይ።

**የግል ወይም ስለ ሌሎች የምንጠይቃቸው የጸሎት ርዕሶች**

1.________________________________________________

2.________________________________________________

3.________________________________________________

4.________________________________________________

5.________________________________________________

ማስታወሻ፡

**ቀን -** ሐሙስ December 3, 2015

**የዕለቱ ንባብ፡** - የሮሜ መልዕክት 12፡ 1 – 21 እና 1 ጴጥሮስ 5፡ 1-10

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ፡** -

1. ከአገልጋዮች እስከ መላው ምዕምን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ቅድስናና ፍቅር የሞላበት ህይወትና አገልግሎት እንዲያቀርቡ እንጸልያለን። (ሮሜ 12፡ 1-2)

2. እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን የአገልግሎት ጸጋንና ሥጦታን እንዳከፋፈለ ሁሉ፤ በቤተክርስቲያንችን ያሉ ቅዱሳን ሁሉ ማንም በጌታ ስራ ስራፈት እንዳይሆን ከጌታ የተቀበሉትን የአገልግሎት ጸጋ በመጠቀም እንዲያገለግሉ እንጸልያለን። በተለይም ከጊዜ አንጻር እንዳያገለግሉ ተግዳሮት ላለባቸው እንጸልያለን። (ሮሜ 12፡ 3 -8)

3. በመካከላችን አብረውን ሲተጉና ሲያገለግሉ የነበሩ በአሁኑ ወቅት ግን በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ከእኛ ጋር ስለሌሉ ወገኖቻችን እንጸልይ። ጌታ ወንድሞችና እህቶቻችን እንዲባርክና መልሶም በመካከላችን በክብሩና በሞገሱ እንዲያቆማቸው፣ ለቤተክርስቲያናችንም በእነርሱ ውስጥ ያለው ጸጋ እንዳይጎልብን እንጸልያለን። (ሮሜ 12፡ 9 -21)

4. ህብረታችንን፣ አምልኮአችንና አገልግሎታችንን የማይወደውን ጠላታችንን በመቃወም በመካከላችን ሥፍራ እንዳይኖረው እያሰርንና እየገሰፅን እንጸልያለን። (1 ጴጥሮስ 5፡ 1-12)

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡** -

1. ስለቤተ ክርስቲያናችን መሪዎች። ጌታ በግል ህይወታቸውና በአገልግሎታቸው እንዲረዳቸው እንጸልያለን።

- ለፓስተር፣ ለቦርድ አፍ ትረስቲ፣ ለቤተክርስቲያንችን ሽማግሌዎች ስለግል ህይወታቸው፣ ስለቤተሰቦቻቸው፣ ስለአገልግሎታቸውና እንዲሁም እርስ በርስ ስላላቸው ፍቅርና አንድነት እንጸልያለን።
- በቤተክርስቲያንችን ያሉትን የአገልግሎት ክፍሎች በመምራት ለሚያገለግሉት ወገኖቻችን የግል ህይወት፣ ቤተሰብ እና አገልግሎት እንጸልያለን።
- በተለያዩ የሚታዩና የምይተዩ የአገልግሎት ክፍሎች ውስጥ ገብተው በትጋት እያገለገሉን ስላሉ የቤተክርስቲያንችን አገልጋዮች የግል ህይወት፣ ቤተሰብ እና አገልግሎት እንጸልያለን።
- በአጠቃላይ አገልጋዮቻችን ሁሉ በቃሉና በጸሎት የጠነከሩ፥ ትጉ እና ምሳሌ የሚሆኑ አገልጋዮች እንዲሆኑ እየጸለይን
- በተጨማሪም ጌታ አገልጋዮችን እንዲያበዛልንና የቤተክርስቲያናችን አባላት ሁሉ የአገልግሎት ተሳትፎ እንዲኖራቸው እንጸልያለን።

2. በቤተክርስቲያናችን ውስጥ በቡድን የሚያገልግሉ የአገልግሎት ክፍሎች ሁሉ እርስ በእርስ በመፈቃቀርና በመከባበር እንዲያገለግሉ እንጸልያለን። በቃል ብቻ ሳይሆን በሥራ እርስ በርስ መዋደድ እንዲበዛልን እንጸልያለን።
3. የአገልግሎት ህብረቶች ለማድከምና ለማጥፋት የሚጥረውን የክፉ መንፈስ አሰራር እንቃወማለን። ሐሜት፥ ራስ ወዳድነት፣ መለያየትንና የመሳሰሉትን ክፉው የሚዘራቸውን ዘሮች በመቃወም እንጸልያለን።
4. የ2016 የቤተክርስቲያን ዋና ራዕይና የአገልግሎት እቅድ የጌታ እጅ ያለበትና ለብዙዎች በረከት እንዲሆን እንጸልያለን።
5. በጃንዋሪ 8, 9, 10, 2016 በቤተክርስቲያናችን ስለሚኖረው ዓመታዊ ኮንፈረንስ እንጸልያለን። ጌታ አገልጋዮችን እንዲልክልንና ይህንንም ኮንፍረንስ ተጠቅሞ የብዙዎችን እንቆቅልሽ እንዲፈታና ጸሎት እንዲመልስ እንጸልያለን። በተጨሪም ይህ ኮንፍረንስ ከቤተክርስቲያናችንም በዙሪያችን ላሉ ሌሎች አብያተክርስቲያናትና ቅዱሳን በረከት እንዲሆን እንጸልያለን።

6. የ2016 የእያንዳንዱ የአገልግሎት ክፍል እቅድ የጌታ እጅ ያለበትና ከዋናው የቤተክርስቲያንም ራዕይና ዕቅድ ጋር የተቀናጀ እንዲሆን እንጸልያለን

## የግል ወይም ስለ ሌሎች የምንጠይቃቸው የጸሎት ርዕሶች

1.________________________________________

2.________________________________________

3.________________________________________

4. _______________________________________

5. _______________________________________

## ማስታወሻ፡

**ቀን** - አርብ December 4, 2015

**የዕለቱ ንባብ፡** - ገላትያ 6፡ 1 – 10 እና የሐዋርያት ሥራ 2፡ 42 – 47 ና 4፡ 32 - 37

**የዕለቱ የጸሎት ርዕሶች ከምንባቡ ፡ -**

1. ከህብረታችን ውስጥ ማንም በሃጢያት ተይዞ እንዳይሰናከል ጌታ እንዲረዳን እንጸልያለን። መሳትና ሃጢያትም ቢከሰት እግዚአብሔር በምህረቱ የንስሃን መንፈስ በመስጠት የሳተን የሚያቀና ልብ፣ ጥበብና ጸጋ ለቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችና ለቅዱሳን ሁሉ እንዲሰጥ እንጸልያለን። (ገላትያ 6፡ 1 – 10)
2. ህብረታችን ከፕሮግራም ያለፈ ህብረት እንዲሆን እንጸልያለን። ሕይወታችንና ኑሮአችን መተሳሰባችን በዝቶ በመካከላችን የሚቸገር ሰው እስከማይኖር ድረስ መዋደድ እንድንችል እንጸልያለን። የሐዋ ሥራ 4፡ 32 - 37

**የቤተክርስቲያን የጸሎት ርዕሶች፡** -

1. ለአገልጋዮችና ለምዕመናን የቅድስናና የፍቅር ህይወት እንጸልያለን።
2. በመካከላችን ሥራ ለሌላቸውና ገንዘብን አስመልክቶ በገቢና በወጫቸው ጠላት ለሚዋጋቸው ወገኖቻችን እንጸልያለን።
3. በመካከላችን በጤና ጉዳይ ለሚቸገሩ ወገኖቻችን ፈውስ እንጸልያለን።
4. የመኖሪያ ቤት ጉዳይ ችግር ለሆነባቸውና ባልተመቸ ሁኔታ ላይ ላሉ ወገኖቻችን እንጸልያለን። እግዚአብሔር ሞገስ ሆኖ እንደቃሉ እንዲያመቻችላቸው እንማልዳለን።
5. በቤተክርስቲያናችን ስላሉ ትዳሮች ሁሉ እንጸልያለን። ትዳሮች እንዲባረኩና ቤቶቻችን በፍቅር ተሞልተው በቤተክርስቲያንና በኢየሱስ መካከል ያለውን አንድነትና ፍቅር የሚያንጸባርቁ እንዲሆኑ እንጸልያለን።
6. ለልጆቻችን መንፈሳዊ ዕድገትና የእግዚአብሔር ጥበቃ እንጸልያለን። እንዲሁም በትምህርታቸው ደግሞ የጌታ እርዳታ እንዲበዛላቸው እንጸልያለን።

7. ባሎቻቸው ወይም ሚስቶቻቸው በአሁኑ ወቅት አብረዋቸው ስለሌሉ ወገኖቻችን እንጸልያለን። ጌታ የመለያየታቸውን ጊዜ አሳጥሮ ጉዳያቸውን ጨርሶ በአንድነት የሚሆኑበትን ነገር እንዲያደርግላቸው እንጸልያለን። በመለያየትም ውስጥ ጸጋውና ጥበቃው እንዲበዛላቸው እንጸልያለን።
8. በቤተክርስቲያንችን ስላሉ ስላላገቡ ወገኖቻችን እንጸልያለን። ጌታ በመልካም ትዳር እንዲባርካቸው እንማልዳለን። በአሁኑ ወቅት በእጮኝነትና ወደ ትዳር በሚያመራ ግንኙነቶች ውስጥ ላሉ ሁሉ ጌታ ጸሎታቸውን እንዲመልስ እንጸልያለን።
9. ቅዱሳን በአስራታችውና በሥጦታቸው ለእግዚአብሔር ታማኝ እንዲሆኑ እንጸልያለን። በኑሮአችን ሁሉ የጌታን ነገር በማስቀደም ያለንን እንዲባርክልን የእርሱ የሆነውን ደግም በፈቃደኝነትና በውዴታ ለቤተክርስቲያን በልግስና በመስጠት የወንጌልን ሥራ እንደሚጠበቅብን መስራት እንድንችል እንዲረዳን እንጸልያለን።

## የግል ወይም ስለ ሌሎች የምንጠይቃቸው የጸሎት ርዕሶች

1.________________________________________

2.________________________________________

3.________________________________________

4.________________________________________

5.________________________________________

**ማስታወሻ፡**